# የስፖርት ማህበራት የበጀት ድጋፍ

# አሰጣጥ መመሪያ

የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር በፌዴራል ደረጃ ለሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራት አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚሰጥ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 917/2008 አንቀጽ 37/1//በ/ ስር የደነገገ በመሆኑ፤

መንግሥት በፌዴራል ደረጃ ለተቋቋሙ የስፖርት ማህበራት በየዓመቱ የበጀት ድጋፍ የሚያደርግ በመሆኑ እና ይህ የድጋፍ በጀት ግልጽና ፍትሀዊ በሆነ የአሰራር ቀመር የሚደለደልበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ማህበራቱ ከመንግሥት የሚያገኙትን የበጀት ድጋፍ ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው አሰራር ለታቀደለት ዓላማ ማዋላቸውን ማረጋገጥ ተገቢ በመሆኑ፤

እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ «የስፖርት ማህበራት የበጀት ድጋፍ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 79/2013» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

1. «የስፖርት ማህበር ወይም ማህበራት» ማለት የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2003 መሰረት በፌዴራል ደረጃ የተቋቋመና በወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ተመዝግቦ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማህበር ነው፡፡

2. «የመደበኛ በጀት ድጋፍ» ማለት ለስፖርት ማህበራት ድጋፍ እንዲውል ከመንግሥት የተመደበና በዚህ መመሪያ የድልድል ቀመር መሰረት ለማህበራቱ የሚመደብ ገንዘብ ነው፡፡

3. «የጨዋታ ዝግጅት ድጋፍ በጀት» ማለት ከመደበኛ በጀት ውጭ ለመላው ኢትዮጵያ ጨዋታዎች ፣ለመላ ኢትዮጵያ ሴቶች ጨዋታዎችና ለመሳሰሉት ኩነቶች የሚመደብ በጀት ነው፡

4. «የበላይ ኃላፊ» ማለት የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይም ሚኒስትር ዴኤታ ነው፡፡

5. «ክልል» ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡

6. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በፌዴራል ደረጃ በተቋቋሙና ከመንግሥት በጀት በሚሰጣቸው የስፖርት ማህበራት ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ መንግሥት ለስፖርት ማህበራት የሚመድበው በጀት ግልጽና ፍትሀዊ በሆነ አሰራር የሚደለደልበትንና ማህበራቱም በጀቱን ግልጽነትና ተጠያቂነት በሰፈነበት ሁኔታ ለታቀደው ዓላማ ማዋላቸው የሚረጋገጥበትን ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የበጀት ድጋፍ አሰጣጥ</u>

### 5. <u>የድጋፍ አሰጣጥ መርህ</u>

የመደበኛ በጀት ድጋፍ እና የጨዋታ ዝግጅት በጀት ድልድልና ክፍፍል መሰረታዊ መርህ በእቅድ አፈጻጸማቸውና በአጠቃላይ እንቅስቃሴያቸው የበለጠ ነጥብ አስመዝግበው የተሻለ ደረጃ የሚያገኙትን ማህበራት የበለጠ ተጠቃሚ በማድረግ ሁሉንም ማህበራት ለተሻለ ውጤት ማነሳሳትን ታሳቢ ያደረገ ይሆናል፡

### 6. <u>የመደበኛ በጀት ድጋፍ ድልድል ቀመር</u>

የስፖርት ማህበራት የመደበኛ በጀት ድልድል ቀመር ማውጫ የማወዳደሪያ መስፈርት ሰንጠረዥ/አንድ/

| ተ.ቁ | የማወዳደሪያ መስፈርት | ነጥብ በፐርሰንት | የነጥብ አሰጣጥ |
|---|---|---|---|
| 1 | በፕሪሚየር ሊግ የሚሳተፉ የወንድና የሴት ክለብ ያለው | 15% | ሁለቱንም ጾታ ያሳተፈ 15%<br>አንድ ፆታ ብቻ ያሳተፈ ከሆነ 10% ያገኛል |
| 2 | በአመት ውስጥ የሚካሄድ የውድድር ብዛት | 15% | 4 እና ከዚያ በላይ ውድድር ያካሄደ 15%፤<br>3 ውድድር ያካሄደ 10%፤<br>2 ውድድር ያካሄደ 5% ያገኛል |
| 3 | የዓለም አቀፍ ተሳትፎ | 10% | 2 ውድድር የተሳተፈ 10%፤<br>ከሁለት በታች የተሳተፈ 5% ያገኛል |
| 4 | ሀብት አሰባሰብ | 10% | በጅቲፒ /GTP/ የተሰጠውን እቅድ ያሳካ 10%፤<br>ግማሽ አፈፃፀም 5%፤ |
| 5 | ታዳጊ ወጣት ፕሮጀክት መያዝ | 10% | በቁጥር ብዛት የሚሰላ |

| ተ.ቁ | የማወዳደሪያ መስፈርት | ነጥብ በፐርሰንት | የነጥብ አሰጣጥ |
|---|---|---|---|
| 6 | የበጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም | 10% | ከ80 በላይ 10%<br>ከ60 እስከ 79 ላከናወነ 5%<br>ከ50 እስከ 59 ላከናወነ 2.5% እያለ የሚቀጥል፡፡ |
| 7 | ወቅቱን የጠበቀ የጠቅላላ ጉባኤ ማካሄድ | 5% | የአመቱን ጠቅላላ ጉባኤ ያካሄደ ሙሉ ነጥብ የሚያገኝ ሆኖ ጉባኤ ላላካሄደ ነጥብ አይሰጥም፡፡ |
| 8 | ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት ማቅረብ | 5% | የኦዲት ሪፖርት ያቀረበ 5% የሚያገኝ ሆኖ ያላቀረበ ነጥብ አይሰጠውም፡፡ |
| 9 | ያቀፋቸው የክልል ስፖርት ፌዴሬሽኖች ብዛት | 5% | ቢያነስ 5 ፌዴሬሽኖችን ላቀፈ 5% የሚሰጠው ሆኖ ከዚያ በታች ላቀፈ አንድ ነጥብ ይቀነስበታል፡፡ |
| 10 | ልዩ ልዩ ስፖርቶችን መያዝ | 15% | ሦስትና ከዚያ በላይ ስፖርቶችን ላቀፉ 15% የሚሰጥ ሆኖ<br>ሁለት ለያዘ 10%<br>አንድ ለያዘ 5 % |

## 6.1 ልዩ ነጥብ

ሀ. የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽን

ለ. የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ እና

ሐ. የኢትዮጵያ ባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን ከላይ ከሚያስመዘግቡት ውጤት ላይ ለእያንዳንዳቸው 30% ይደመርላቸዋል፡፡

## 7. የጨዋታ ዝግጅት በጀት ድጋፍ

የስፖርት ማህበራት የጨዋታ ዝግጅት የበጀት ድልድል ቀመር ማውጫ የማወዳደሪያ መስፈርት ሰንጠረዥ/ሁለት/

| ተ.ቁ | ማወዳደሪያ መስፈርት | ነጥብ በፐርሰንት | የነጥብ አሰጣጥ |
|---|---|---|---|
| 1 | የጨዋታው ጊዜ ቆይታ | 15% | በስታንዳርዱ መሰረት የሚሰላ |
| 2 | የቴክኒክ ኮሚቴ አባለት ብዛት ቁጥር ማነስ | 10% | በቁጥር የሚለካ |
| 3 | ጨዋታውን የሚመሩ ዳኞች ብዛት | 10% | በስታንዳርዱ መሰረት የሚሰላ |
| 4 | የተሳታፊ ቡድኖች ብዛት | 10% | ከፍተኛ ቁትር ለያዘ ሙሉ ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ ከሱ በታች ለያዙ እየቀነሰ የሚሄድ ይሆናል |
| 5 | ተሳታፊ ስፖርተኞች ብዛት | 10% | |
| 6 | የዝግጅት ዙር ብዛት | 5% | በስታንዳርዱ መሰረት የሚረጋገጥ |
| 7 | ክልሎችን ያሳተፈ የዳኞች ምርጫ ማካሄድ | 5% | የአብዛኛው ክልሎች ተሳትፎ መኖሩ ሲረጋገጥ |
| 8 | ከዚህ ቀደም ወሰደውን የድጋፍ በጀት አጠቃቀም በተመለከተ የሂሳብ ሪፖርት ያቀረበ | 10% | ወቅቱን የጠበቀ ሪፖረት ላቀረበ ሙሉ ነጥብ ይሰጣል፡፡ ማዘግየት ፣አለማቅረብ እንደሁኔታው የሚያስቀንስ ይሆናል |
| 9 | የትክኒክ ኮሚቴ አባለትንና የዳኞችን ሥም አስቀድሞ ማቅረብ | 5% | በተጨቀው ቀን ላቀረበ ሙሉ ነጥብ የሚሰጥ ሆኖ ላዘጌ እተቀነሰበት የሚሄድ |
| 10 | ለቁሳቁስና መሳሪያዎች ማጓጓዣ ማቅረብ | 5% | ያቀረበ ሙሉ ነትብ |
| 11 | የውድድር ደንብ በተባለው ጊዜ ውስጥ ማቅረብ | 10% | በወቅቱ ላቀረበ ሙሉ ነጥብ ሚሰጥ ሆኖ ላዘገየ እየቀነሰ ሚሄድ |
| 12 | የልምምድና የውድድር መርሃግብር ዝግጅት | 5% | አስቀድሞ ላቀረበና ጥራቱን ለጠበቀ ሙሉ ነጥብ የሚሰጥ ሆኖ ላዘጌ እየቀነሰ ሚሄድ |

7.1 **ልዩ ነጥብ**

ሀ. የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽን

ለ. የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ እና

ሐ. የኢትዮጵያ ባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን ከላይ ከሚያስመዘግቡት ውጤት ላይ ለእያንዳንዳቸው 10% ይደመርላቸዋል፡፡

2. የጨዋታ ዝግጅት በጀት ድጋፍ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ተወዳድረው በሚያገኙት ነጥብ መሰረት የሚደለደል ይሆናል፡፡

## 8. የስፖርት ማህበራት ደረጃ

1. ለድልድሉ ዓላማ ሲባል የስፖርት ማህበራት ቀደም ሲል ባላቸው አፈጻጸም በሚያገኙት ነጥብ መሰረት እንደሚከተለው በሦስት ደረጃዎች ይመደባሉ፡፡

ሀ. አንደኛ ደረጃ ከ70% በላይ ያገኘ

ለ. ሁለተኛ ደረጃ ከ60% እስከ 69% ያገኘ

ሐ. ሦስተኛ ደረጃ ከ59% በታች ያገኘ

2. የድጎማ በጀት በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8 መሠረት ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ደረጃ ለሚመደቡ የስፖርት ማህበራት እንደሚከተለው ይመደባል፤

ሀ. ለአንደኛ ደረጃ 53%

ለ. ለሁለተኛ ደረጃ 27%

ሐ. ለሦስተኛ ደረጃ 20%

9. <u>የበጀት ድጋፍ መጠየቂያ ቅጽ ሞልቶ ስለማቅረብ</u>

የበጀት ድጋፍ እንዲሰጠው የሚፈልግ የስፖርት ማህበር የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የሚያሰራጨውን የድጎማ በጀት ድጋፍ መጠየቂያ ቅጽ በመሙላት ለዳይሬክቶሬቱ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

10. <u>የበጀት ድልድል ቀመር አወሳሰን</u>

1. በየበጀት ዓመቱ ለተቋሙ የተመደበው በጀት እንደታወቀ፤
   - ሀ. የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶራት
   - ለ. የስፖርት ማህበራት እውቅና እና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
   - ሐ. የስፖርት ተሳትፎና ውድድር ዳይሬክቶሬት
   - መ. በአገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት የተወከሉ አራት አባላት በጋራ በመሆን፣

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 እና አንቀጽ 7 ሥንጠረዥ ስር በተመለከተው የማወዳደሪያ መስፈርት መሰረት የሚያገኙትን ውጤት መሰረት አድርገው ለማህበራቱ ይደለድላሉ፡፡

2. ድልድሉ እንደተጠናቀቀ የእያንዳንዱ የስፖርት ማህበር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 እና 7 ስር የተቀመጠውን የማወዳደሪያ መስፈርት መሰረት አድርጎ ያገኘው ነጥብ፡ እና የተመደበለት በጀት በይፋ ይገለጽለታል፡፡
3. ከአጠቃላይ የድጎማ በጀቱ 53 በመቶ የሚመድብላቸው አንደኛ ደረጃ ማህበራት፤
   - ሀ. የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ኮሚቴ፤
   - ለ. የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን
   - ሐ. የኢትዮጵያ ባህል ስፖርት ፌዴሬሽን፤
   - መ. የኢትዮጵያ ወርልድ ቴኳንዶ ፌዴሬሽን፤
   - ሠ. የኢትዮጵያ ቮሊቦል ፌዴሬሽን፤
   - ረ. የኢትዮጵያ ቦክስ ፌዴሬሽን፤
   - ሰ. የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ፌዴሬሽን፤
   - ሸ. የኢትዮጵያ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን፤

4. ከአጠቃላይ የድጎማ በጀቱ 27 በመቶ የሚመድብላቸው ሁለተኛ ደረጃ የስፖርት ማህበራት፤

ሀ. የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽን፤

ለ. የኢትዮጵያ ብስክሌት ፌዴሬሽን፤

ሐ. የኢትዮጵያ ባድሚንተን ፌዴሬሽን፤

መ. የኢትዮጵያ ጠረጴዛ ቴንስ ፌዴሬሽን፤

ሠ. የኢትዮጵያ ጅምናስቲክ ፌዴሬሽን፤

ረ. የኢትዮጵያ ክብደት ማንሳትና ሰውነት መገንባት ፌዴሬሽን፤

ሰ. የኢትዮጵያ ሜዳ ቴንስ ፌዴሬሽን፤

ሸ. የኢትዮጵያ ካራቴ ፌዴሬሽን፤

ቀ. የኢትዮጵያ ቼስ ፌዴሬሽን፤

በ. የኢትዮጵያ ውኃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን፤

ተ. የኢትዮጵያ ውሹ ፌዴሬሽን፤

5. ከአጠቃላይ የድጎማ በጀቱ 20 በመቶ የሚመድብላቸው ሦስተኛ ደረጃ ማህበራት፣

ሀ. የኢትዮጵያ ቦዉሊንግ ስፖርት አሶሴሽን፤

ለ. የኢትዮጵያ ሞተር ስፖርት አሶሴሽን፤

ሐ. የኢትዮጵያ ጎልፍ ስፖርት አሶሴሽን፤

መ. የኢትዮጵያ ፈረስ ስፖርት አሶሴሽን፤

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

11. **ስለ ቁጥጥር**

1. በዚህ መመሪያ መሰረት የበጀት ድጋፍ የተሰጠው ማንኛውም የስፖርት ማህበር ስለበጀቱ አጠቃቀም የአፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ ለግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፡፡

2. የመስሪያ ቤቱ የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በዚህ መመሪያ መሰረት የተሰጠው የበጀት ድጋፍ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን እየመረመረ የደረሰበትን ውጤት ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፡፡

12. <u>**መመሪያውን ስለማሻሻል**</u>

ይህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው ሊሻሻል ይችላል፡፡

13<u>. **መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**</u>

ይህ መመሪያ ከታህሳስ 13 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ርስቱ ይርዳ

ሚኒስትር